# የምዝገባ መረጃ

**የመመዝገቢያ 3 ቀላል ዘዴዎች!** **የአሌክሳንደሪያ ከተማ ምዝገባ ረቡዕ፣ መጋቢት 18 በ9 am ሰዐት ይጀምራል**
**ነዋሪ ያልሆኑ ተመዝጋቢዎች ምዝገባ አርብ፣ መጋቢት 20 በ9 am ሰዐት ይጀምራል**

### ድረገጽ

- ክፍያ በክሬዲት ካርድ (Visa/MC) ወይም eCheck ይከፈላል
- alexandriava.gov/Recreationን ይጎብኙ
- የምዝገባ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 703.746.5414 ይደውሉ በ የኢሜይል መልዕክት ይላኩ

### በአካል ማስገቢያ

ሊ ሴንተር/Lee Center, 1108 Jefferson St.፤ በአካል ማስገቢያ ምዝገባዎች የሚገቡበት ቀንና ሰአት ምንም ይሁን ምን በምዝገባ መክፈቻ ቀን ለመስተናገድ ይወጣሉ። በአካል ማስገቢያ ምዝገባ ለክፍል/ፕሮግራም ምዝገባ ዋስትና አይሰጥም

### በመልዕክት መላኪያ

- ሊ ሴንተር/Lee Center, 1108 Jefferson St., Alexandria, VA 22314
- የተሞላ የምዝገባ ቅጽ ከላይ በተገለጸው አድራሻ ይላኩ።
- ቼኮች በ "አሌክሳንደሪያ ከተማ/City of Alexandria." ገጾች እንዲከፈሉ ያድርጉ።
- የመልዕክት ምዝገባ ለመስተናገድ እስከ አምስት (5) የስራ ቀናት ይወስዳል።

**አገልግሎቶች**: የአሌክሳንደሪያ ከተማ ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶችና አገልግሎት መስጫዎች የዘር ሀረግ፣ ቀለም፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ጾታ፣ እድሜ ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት ሳያደርጉ ለሁሉም ዜጎች ይቀርባሉ። የአሌክሳንደሪያ ከተማ ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች የአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች ሕግን ያከብራል። የADA የአገልግሎት ጥያቄ ለማቅረብ እባክዎ ከዝግጅት፣ ተገባር ወይም የምዝገባ ማብቂያ ቀን ከሁለት ሳምንታት በፊት በስልክ ቁጥር 703.746.4343 ወይም VA Relay 711 ይደውሉ። ጥያቄዎን በማቅረብ ላይ እገዛ ማግኘት ካስፈለግዎ ወይም ስለ አገልግሎት አይነቶች በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎ እባክዎ ለህክምና መዝናኛ ጽ/ቤት /Therapeutic Recreation Office በስልክ ቁጥር 703.746.5422 ወይም VA Relay 711 ይደውሉ። የአሌክሳንደሪያ ከተማ የመዝናኛ፣ ፓርኮችና የባህል ተግባሮች መምሪያ ብሪይልን ጨምሮ የሚቀርቡለትን ለጽሁፍ ሰነዶች አማራጭ ፎርማቶች ጥያቄዎች ጥያቄው በቀረበ በአስር ቀናት ውስጥ ማሟላት አለበት።

**የተመላሽ/ብድር ፖሊሲ:**
ተመዝጋቢዎች በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ ተመስርተው ለፕሮግራሞች የተመላሽ ወይም የቤተሰብ ብድር ጥያቄ በጽሁፍ ለአይ ሊ ሴንተር/ Lee Center, 1108 Jefferson St., Alexandria, VA 22314 ሊያቀርቡ ወይም በregisterarpca@alexandriava.gov በኢሜይል ሊልኩ ይችላሉ:

- ሙሉ ብድሮች በመምሪያው ለሚሰረዙ ተግባሮች ይታያሉ። የሚመርጡት ተመላሽ ከሆነ እባክዎ ይህን ያሳውቁን።
- በክፍል/ፕሮግራም የማይረኩ ተመዝጋቢዎች ማስተካከያ ለማድረግ እንዲያስችለን በአፋጣኝ RPCAን እንዲያናግሩ ይበረታታሉ። ጉዳዩን ማስተካከል ካልቻልን ብድር ወይም ተመላሽ ልንሰጥ እንችላለን።
- አድራሻ በመቀየር፣ የመርሀግብር መጋጨት፣ በህመም ወይም ጉዳት የተነሳ በፕሮግራም ላይ መገኘት የማይችሉ ተመዝጋቢዎች ብድር ወይም ተመላሽ ሊጠይቁ ይችላሉ።
- ብድሮች በቤተሰብ ሂሳብ ላይ ከ90 ላልበለጠ ቀናት ይቆያሉ። ከ90 በላይ የሚቆዩ ብድሮች ለደንበኛው እንደተመላሽ ለመመለስ ይስተናገዳሉ።
- የአዋቂ ሊግ ክፍያዎች ተመላሽ አይደረጉም።

**ስረዛዎች**: ዝቅተኛ የተመዝጋቢዎችን ብዛት የማያሟሉ ክፍሎች ከመጀመሪያ ቀን ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ይሰረዛሉ። ለተሳታፊዎች ስለተሰረዙ ክፍሎች በስልክ ወይም በኢሜይል ይገለጽላቸዋል።

**የክፍል ስፋት**: የተሳታፊዎች ዝቅተኛና ከፍተኛ ብዛት የሚወሰነው በአንድ መምህር/ኢንስትራክተር ላይ ተመስርቶ ነው። መምህራን/ኢንስትራክተሮች የሚጨምሩ ከሆነ የክፍል ስፋቱ ሊጨምር ይችላል።

**ማረጋገጫ**: ከድረገጽ ውጭ ተመዝጋቢዎች በመልዕክት ማረጋገጫ ይላክላቸዋል። በመልዕክት ማረጋገጫ የማይደርስዎት ከሆነ እባክዎ የምዝገባ ማረጋገጫ ለማግኘት ይደውሉልን።

**የአካል ምዝገባዎች**: በሊ ሴንተር/ Lee Center የማስገቢያ ሳጥን ውስጥ በአካል የሚከተቱ የምዝገባ ቅጾች ለመስተናገድ እስከ አምስት (5) የስራ ቀናት ይወስድባቸዋል።

**ክፍያዎች**: ሁሉም ክፍያዎች በሙሉ እና በምዝገባ ወቅት መከፈል አለባቸው። ከፊል ክፍያ ለምዝገባ አያገለግልም። ሁሉም በግለሰብ ስም የሚጻፉ ቼኮችና የገንዘብ ማዘዣዎች "ለአሌክሳንደሪያ ከተማ/City of Alexandria." ይከፈላሉ። ለቤተሰብ ምዝገባዎች አንድ ቅጽና ቼክ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ክፍያዎች ያለ ማስታወቂያ ለውጥ ሊደረግባቸው ይችላል።

**እርዳታ ለማግኘት**: ፖሊሲ ለማየትና የፋይናንስ ድጋፍ መጠየቂያ ቅጽ ለመግኘት alexandriava.gov/12288ን ይጎብኙ

**አስገዳጅ ሁኔታ**: ፖሊሲውን ለማየት alexandriava.gov/Recreationን ይጎብኙ

**ነዋሪ ያልሆነ ተመዝጋቢ ክፍያ**: ለሁሉም የክፍል ክፍሎች ከክፍል ክፍያ በተጨማሪ በሰው $35 ክፍያ መከፈል ያስፈልጋል። ይህ ክፍያ ክፍል/ተግባር በመዝናኛ፣ ፓርኮችና የባህል ተግባሮች መምሪያ ካልተሰረዘ በስተቀር ተመላሽ አይደረግም።

**የመዝናኛ ማዕከል የመታወቂያ ፖሊሲ**: በመኖሪያ መንደር የመዝናኛ ማዕከላት ለመመዝገብ የነዋሪነት ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል። ሁሉም እድሜያቸው 13 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተሳታፊዎች ወደ የመኖሪያ መንደር የመዝናኛ ማዕከላት ለመግባት የመዝናኛ ማዕከል ፎቶ ያለው መታወቂያ (የመጀመሪያ መታወቂያ ያለ ክፍያ ይሰጣል) ያላቸው መሆን አለባቸው። የመታወቂያ ካርዶች የሚያገለግሉት ለአንድ አመት (ከሀምሌ እስከ ሰኔ) ሲሆን መታወቂያውን በየአመቱ ለማደስ የነዋሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ያስፈልጋል። የመታወቂያ ካርዶችን ለመቀየር $5 ክፍያ ይከፈላል። የከተማ ነዋሪነትን ማረጋገጫ ተቀባይነት ያላቸው የመታወቂያ አይነቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

1. ወቅታዊ የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት አገልግሎቱ ያላበት የVA የአሽከርካሪነት ፍቃድ፤
2. አገልግሎቱ ያላበት ፎቶ የያዘ መታወቂያ ከወቅታዊ ኪራይ፣ በከተማ የተሰጠ ሰነድ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ጋር፤ ወይም
3. አገልግሎቱ ያላበት የአሌክሳንደሪያ ትምህርት ቤት መታወቂያ (ለተማሪዎች) እና የወላጅ የነዋሪነት ማረጋገጫ። የወላጅ ነዋሪነት ከላይ በተገለጸው መሰረት ሊጣራ ይችላል።

**የመጠቀም ፍቃድ**: በመዝናኛ፣ ፓርኮችና የባህል ተግባሮች መምሪያ ስፖንሰር የሚደረጉ ወይም በተብብር ስፖንሰር የሚደረጉ ተግባሮች ተሳታፊዎች ለከተማው የተግባሩን የትኛውንም ፎቶግራፍ፣ ፊልም ወይም የቪዲዮ ቅጂ በየትኛውም የገበያ ወይም ማስተዋወቂያ ህትመት ላይ መጠቀም የሚችሉበት ፍቃድ ይሰጣሉ።

**የአረጋውያን ቅናሽ**: እድሜያቸው 55 አመትና ከዚያ በላይ የሆኑ የከተማ ነዋሪዎች ለሁሉም ክፍሎች በድረገጽ ሲመዘገቡ ወዲያውኑ 20% ቅናሽ ይደረግላቸዋል።

**የህክምና መዝናኛ**: ተሳታፊዎች የግል የትምህርት እቅድ (IEP) ወይም የ504 እቅድ ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል። በፕሮግራሞች ላይ ተሳትፎ ከመደረጉ በፊት ለሁሉም ፕሮግራሞች የመጀመሪያ ምዘና ማካሄድና የብቃት ፍቃድ ማግኘት ይጠየቃል። ለመመዝገብ በስልክ ቁጥር 703.746.5422 ይደውሉ።

**የተጠባባቂ ዝርዝር**: ክፍል ሙሉ ከሆነ የተጠባባቂ ዝዝርዝር ይዘጋጃል እንዲሁም በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ከተመዘገቡ ግለሰቦች ጋር ቦታ ሲገኝ ግንኙነት ይደረጋል።

**ለውጥ**: ክፍያዎች፣ ፕሮግራሞችና ሰአቶች ለውጥ ሊደረግባቸው ይችላል። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት alexandriava.gov/Recreationን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 703.746.4343 ይደውሉ።

# የምዝገባ ቅጽ

ጥያቄዎች አሉዎ? በስልክ ቁጥር 703.746.5414 (ከሰኞ-አርብ ከ9 am-7 pm ሰዐት)፣ VA Relay 711 ይደውሉ ወይም በ **registerarpca@alexandriava.gov** ኢሜይል ይላኩ

የምዝገባ መጀመሪያ ቀን: መጋቢት 18 (ለነዋሪዎች) & መጋቢት 20 (ነዋሪ ያልሆኑ)

## ❶ የቤተሰብ መረጃ- እባክዎ ያትሙ *አስፈላጊ መረጃ የተመላሽ ፖሊሲ በቀዳሚው ገጽ የምዝገባ መረጃ ስር ተካቷል።

* የቤተሰብ ኃላፊ ስም (የመጀመሪያ/የመጨረሻ) ______________ የሚከተሉት ለውጥ ካለ ምልክት ያድርጉ ☐ አድራሻ ☐ ስልክ ☐ ኢሜይል – የተፈጻሚነት ቀን ______________

* አድራሻ ______________ * ከተማ፣ ግዛት፣ ዚፕ ______________

* የመኖሪያ ቤት ስልክ ______________ የስራ ቦታ ስልክ ______________ የሞባይል ስልክ ______________

* የቤተሰብ ኃላፊ የትውልድ ቀን ________/________/________ * ወንድ/ሴት ነዎት? (ያክብቡ) የኢሜይል አድራሻ ______________

## ❷ የተግባር ምዝገባ (እባክዎ ሙሉ በሙሉ ይሙሉ። አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ቅጽ ያያይዙ)

| የተሳታፊ ስም | ጾታ ወ/ሴ | የትውልድ ቀን | የተግባር መጠሪያ | የተግባር # | የመጀመሪያ ቀን | ክፍያ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| *የጆይ/Joey ናሙና* | *ወንድ* | *1/2/12 ዓ.ም* | *የእግር ኳስ መጫወቻ* | *422610-01* | *1/18/18 ዓ.ም* | *$169* |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

| | |
|---|---|
| ጠቅላላ የተዘረዘሩ ክፍያዎች | |
| የሂሳብ ብድሮች/ቅናሾች ይቀንሱ– | |
| ነዋሪ ያልሆነ ተመዝጋቢ ክፍያ (በየተግባር ለእያንዳንዱ $35) + | |
| ልገሳ + | |
| **ድምር** (ይህን የገንዘብ መጠን ይክፈሉ) | |

**የምዝገባ ማብቂያ ጊዜ** - ዝቅተኛውን የተመዝጋቢ ብዛት የማያሟሉ ክፍሎች ከመጀመሪያ ቀን ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ይሰረዛሉ። ለተሳታፊዎች ስለተሰረዙ ክፍሎች በስልክ ወይም በኢሜይል ይገለጽላቸዋል እንዲሁም ተመላሽ ወይም ዝውውር ካልተጠየቀ በስተቀር ብድር ይሰጣቸዋል። እባክዎ ለተመላሽ ከ3-4 ሳምንታት ይፍቀዱ።

**ቼኮች ለ "አሌክሳንደሪያ ከተማ/City of Alexandria" እንዲከፈሉ ያድርጉ።**

## ❸ እባክዎ ከዚህ በታች አንብበው ይፈርሙ:

**ከጉዳት ነጻ የማድረግ ስምምነት:** የአሌክሳንደሪያ ከተማ፣ የመዝናኛ፣ ፓርኮችና የባህል ተግባሮች መምሪያ የተለያዩ ፕሮግራሞችን እያካሄደ እንደሆነና ከላይ የተጠቀሱትን በእነዚህ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ የፈቀድ መሆኑን በመገንዘብ እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት በእነዚህ ፕሮግራሞች ተሳታፊ ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት ስጋትን በመረዳት ፕሮግራሞቹ እየተካሄዱ ባሉበት ወቅት በፈራሚው ወይም በገራሚው ልጅ ምክንያት በሚደርስ ወይም ሊደርስ በሚችል የትኛውም የአካል ጉዳት ወይም የንብረት ጉዳት የተነሳ ከሚፈጠሩ ከየትኛውም እና ሁሉም የካሳ ጥያቄዎች ወይም ተጠያቂነት የአሌክሳንደሪያ ከተማ፣ የመዝናኛ፣ ፓርኮችና የባህል ተግባሮች መምሪያን እና ኦፊሰሮቹን፣ ወኪሎቹን እና ሰራተኞቹን አሁንም ሆነ ለወደፊት ከኃላፊነት ነጻ ማድረጌን አረጋግጣለሁ።

**የአዋቂ ተሳታፊ፣ የህጻን ወላጅ ወይም አሳዳጊ ፊርማ ያስፈልጋል** **ቀን**

**የምዝገባ ቅጾች ሊመለሱና በክፍል ምዝገባ ላይ ተጽኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ**

**ለከተማ ነዋሪዎች የሚቀርብ የክፍያ ድጋፍ ፕሮግራም**

የመዝናኛ፣ ፓርኮችና የባህል ተግባሮች መምሪያ ሁሉንም የከተማዋን ነዋሪዎች በከተማዋ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል። እርስዎ፣ የቤተሰብዎ አባል ወይም ጓደኛዎ በመምሪያው ስፖንሰር በሚደረጉ ፕሮግራሞች ወይም ተግባሮች ላይ ለመሳተፍ የምትፈልጉ ከሆነ እና ለመሳተፍ የክፍያ ድጋፍ ማግኘት የምትፈልጉ ከሆነ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ቢያንስ ከሁለት ሳምንታት አስቀድማችሁ የስፖንሰር አድራጊው ፕሮግራም ጽ/ቤትን እንድታናግሩ እንመክራችኋለን። ጠቅላላ መረጃ ለማግኘት እባክዎ በስልክ ቁጥር 703.746.4343 ይደውሉ ወይም VA Relay 711ን ይጠቀሙ።

## ❹ የምዝገባ ዘዴ

**በመልዕክት ወይም በአካል ማስገባት:**
ምዝጋባና ቦታ ማስያዣዎች/Registration & Reservations/Lee Center 1108 Jefferson St., Alexandria, VA 22314

**ድረገጽ:**
alexandriava.gov/Recreation

**ጥያቄዎች አሉዎ?**
በስልክ ቁጥር 703.746.5414 ይደውሉ
በ registerARPCA@alexandriava.gov የኢሜይል መልዕክት ይላኩ።

**ለጽ/ቤት ግልጋሎት ብቻ:**

የቼክ #: ______ የገንዘብ መጠን: ______

የተከፈለበት ቀን: ______ ተቀባይ ሰራተኛ: ______